የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ — ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 12
ADDIS ABABA - 17th December, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፶፭/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

አስትሪያ ፣ ፊንላንድና ስዊድን የሎሜ አራት ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች የሆኑበት የፕሮቶኮል ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፪፻፺፬

## CONTENTS

Proclamation No. 55/1996

Ratification of the Protocol on the Accession of Austria, Finland and Sweden to the Fourth Lome Convention Proclamation .......................... Page 294

### አዋጅ ቁጥር ፶፭/፲፱፻፹፱
### አስትሪያ ፣ ፊንላንድና ስዊድን የሎሜ አራት ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች የሆኑበትን የፕሮቶኮል ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

አስትሪያ ፣ ፊንላንድና ስዊድን እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ጀምሮ የአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገሮች ስለሆኑ ፤

የአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገሮች በአንድ በኩል እንዲሁም ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካ ፣ የካሪቢያንና የፓስፊክ ሀገሮች ቡድን በሌላ በኩል ሆነው የተጠቀሱትን ሦስት ሀገሮች የሎሜ አራት ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በማድረግ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ሞሪሽየስ ላይ የፕሮቶኮል ስምምነት ስለተፈራረሙ ፤

የፕሮቶኮል ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ተፈራራሚዎቹ ሀገሮች ሲያጸድቁት በመሆኑ ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕሮቶኮል ስምምነቱን ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### PROCLAMATION NO. 55/1996
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE PROTOCOL ON THE ACCESSION OF AUSTRIA, FINLAND AND SWEDEN TO THE FOURTH LOME CONVENTION

WHEREAS, Austria, Finland and Sweden became Member States of the European Union on January 1,1995;

WHEREAS, Ethiopia is one of the parties to the Protocol, on the accession of the aforementioned three States to the Fourth Lome Convention, signed in Mauritius on December 8 1995 between African, Caribbean and Pacific States, on the one hand, and Member States of the European Union, on the other;

WHEREAS, the Protocol enters into force subject to ratification by the signatory States;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Protocol at its session held on the 17th day of December, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub–Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ "አስትሪያ ፣ ፊንላንድና ስዊድን የሎሜ አራት ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች የሆኑበት የፕሮቶኮል ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፶፭/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>
አስትሪያ ፣ ፊንላንድና ስዊድንን የሎሜ አራት ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በማድረግ በአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገሮች እና በአፍሪካ ፣ ካሪቢያንና ፓስፊክ ሀገሮች ቡድን መካከል እ·ኤ·አ· ዲሴምበር ፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ሞሪሽየስ ላይ የተፈረመው የፕሮቶኮል ስምምነት ጸድቋል ።

፫· <u>የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>
የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የፕሮቶኮል ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Ratification of the Protocol on the Accession of Austria, Finland and Sweden to the Fourth Lome Convention Proclamation No. 55/1996."

2. *Ratification of the Protocol*
The Protocol on the Accession of Austria, Finland and Sweden to the Fourth Lome Convention signed in Mauritius on December 8, 1995 between ACP States and Member States of the European Union is ratified.

3. *Power of the Ministry of Economic Development and Cooperation*
The Ministry of Economic Development and Cooperation is hereby empowered to implement the Protocol.

4. *Effective Date*
This proclamation shall enter into force as of the 17th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 17th day of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE